# አማርኛ

> AMHARIC

U.S. CAPITOL
የጉብኝት ማዕከል

# የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል ጉብኝት

## ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል እንኳን ደህና መጡ

### ጠቅላላ የጉብኝት መረጃ

- በአስጎብኚ በመታገዝ የሚካሄደው የካፒቶል ታሪካዊ ጉብኝት የሚጀምረው በአንድ አጭር የመግቢያ ፊልም ነው። ጉብኝቱ የሚካሄደው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው ሆኖም ግን የፊልሙን ትርጉም በሌሎች ቋንቋዎች ለመከታተል የሚያግዙ የጆሮ ማዳመጫዎች ከሰሜንና ከደቡብ የመረጃ ዴስኮች ማግኘት ይችላሉ።
- የካፒቶልን ደህንነትና የተጠበቀ መሆን ለማረጋገጥ በጉብኝቱ ወቅት ሁሉ ከተመደበልዎ የጉብኝት መሪ ጋር አብረው መቆየት **አለብዎ**።
- በጉብኝቱ ላይ ምንም የህዝብ ሽንት ቤቶች አይኖሩም። እባክዎ የማስተዋወቂያ ፊልሙን ለመመልከት ከመግባትዎ በፊት በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ውስጥ ካሉት በርካታ ሽንት ቤቶች በአንዱ ይጠቀሙ።
- በጉብኝቱ ወቅት ማናቸውንም ሀውልቶችና ስእሎች በአይንዎ ብቻ በመመልከት ያድንቁ ሆኖም ግን እባክዎ በእጅዎ ከመንካት ይቆጠቡ።
- በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ውስጥ ለእርስዎ ግልጋሎት የተዘጋጁ በርካታ መቀመጫዎች ያሉ በመሆኑ — እባክዎ ወለሉ ላይ አይቀመጡ።
- በማንኛውም ምክንያት የህክምና እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እባክዎ ምንም ሳያመነቱ ለጉብኝት መሪዎ ወይም ለዩኤስ ካፒቶል ፖሊስ መኮንን ያሳውቁ።

**ይህ በእራስ መሪነት የሚካሄድ ጉብኝት አይደለም።**

በጉብኝትዎ ጊዜ ሁሉ እባክዎን ከጉብኝት መሪዎ ጋር ይቆዩ።



የዩኤስ ካፒቶል ጉብኝት ተጀምሮ እስከሚያልቅ **ከጥቂት ቦታዎች በስተቀር ፎቶ ግራፍ ማንሳት ይፈቀዳል።** በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት በትእይንት አዳራሽ ወይም በገለጻ ቲያትር ውስጥ ፎቶ ከማንሳት ይቆጠቡ። **ፎቶ ግራፍ ለማንሳት ከቡድንዎ ተነጥለው መሄድ የለብዎትም።** የጉብኝት መሪዎ ጉብኝቱን በዩኤስ ካፒቶል ፖሊስ የተዘጋጀውን መስመር ተከትለው እንዲያካሂዱ ተነግሯቸዋል።



በዓለም ዙሪያ በዲሞክራሲ አስተዳደር ምልክትነቱ በሰፊው የሚታወቀው የዩኤስ ካፒቶል ከ1800 ዓም ጀምሮ የሸንጎው መስሪያ ቤት ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

የአገሪቱን ሕግጋቶች ለማርቀቅ ሸንጎው የሚሰበሰብበት እና ፕሬዝዳንቶች ስልጣን የሚረከቡበት ሥርዓት የሚካሄድበት እንዲሁም የአገር አንድነትን በሚመለከት መልክት የሚያስተላልፉት በዚሁ በካፒቶል ነው።

ለሁለት ክፍለ ዘመናት አዲስ ክፍለ ግዛቶች በተደባለቁ ቁጥር የአዲሶቹ ግዛቶች ተወካዮች እና ሴኔተሮችን ለማስተናገድ የካፒቶል ህንፃ አዲስ ክንፍ በመጨመር ከአገሪቱ ጋር አብሮ እያደገ ይገኛል።

ጣሪያዎቹ በታሪካዊ ስዕላት ያጌጡ ሲሆን፤ መተላለፊያዎቹም የአገሪቷን ታላላቅ ክስተቶች እና ሕዝቦች በሚዘክሩ ሃውልቶች እና ስዕሎች ያጌጡ ናቸው።

## ክሪፕት



በካፒቶል አንደኛ ወለል ላይ የሚገኘው ሰፊ ክብ ቤት **ክሪፕት** ተብሎ ይጠራል። 40ዎቹ ዶሪክ ምሰሶዎች በሸክላ አፈር የተሰሩ ሆነው ከአናታቸው በሸክላ አፈር ቅስቶች እርስበርስ ተያይዘው ለሮተንዳው ወለል ድጋፍ ይሰጣሉ። ይህ የህንጻው ማእከላዊ ክፍል ተሰርቶ የተጠናቀቀው በ1827 ዓ.ም ነው። በወለሉ ማእከላዊ ክፍል ላይ የሚገኘው ኮከብ የዋሽንግተን ዲሲ መንገዶች መነሻ አድርገው የተሰሩበትን እና ቁጥር ያገኙበትን ነጥብ ይወክላሉ።



በክሪፕቱ ውስጥ ከብሄራዊ የሀውልቶች አዳራሽ ስብስብ የመጡ 13 ሀውልቶች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ሀውልቶች የመጀመሪያዎቹን 13 ቅኝ ግዛቶችን የሚወክሉ ናቸው።



በሳውዝ ዳኮታ ግዛት ውስጥ ማውንት ረሽሞር በመባል በሚታወቅ ተራራ ላይ ሀውልት በመቅረጽ በሚታወቀው ጉትዞን ቦርግለም የተቀረጸው የአብርሀም ሊንኮልን የአንገት በላይ ሀውልት



ክሪፕት በመባል በሚታወቀው ቤት ውስጥ የሚገኘው የማግና ካርታ ቅጅ የዩናይትድ ስቴትስ ህገ መንግስት የተቀረጸበትን መርሆዎች የያዘ የእንግሊዝ ሰነድ ነው። ጠቅላላ ማሳያው የተሰራው እንግሊዝ አገር ውስጥ በአርቲስት ልዊስ ኦስማን ሲሆን አሜሪካ የሁለት መቶ አመት የነጻነት መታሰቢያዋን ለማክበር እንዲያገለግል በእንግሊዝ መንግስት በ1976 በስጦታነት የተሰጠ ነው።

## ሮተንዳ

**የካፒቶል ሮተንዳ** 96 ጫማ የክበብ አጋማሽ ስፋትና 180 ጫማ ቁመት ያለው ክብ ክፍል ሆኖ በካፒቶሉ ህንጻ መካከል ላይ ይገኛል። ሮተንዳው ታዋቂ የሆኑ ዜጎች በሚሞቱበት ግዜ አስከሬናቸው ለስንብት በክብር የሚያርፍበትና የሥነ ጥበብ ስራዎችን ለማስቀመጥና ለመሳሰሉ አስፈላጊ የክብረ በአል ዝግጅቶች ያገለግላል። የጉልላቱ ጣሪያ በኢጣሊያ አሜሪካዊው የኪነ ጥበብ ባለሙያ ኮንስታንቲኖ ብሩሚዲ ‹‹ዘ አፖቲዮሲስ ኦፍ ዋሽንግተን›› በሚል ርእስ በኖራና በጄሶ የተሰሩ የጣሪያ ላይ ስእሎች አሉት። በሮተንዳው የውስጥ ክፍል በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ክስተቶችን የሚገልጹ ታሪካዊ ስእሎችና በኖራና በጄሶ የተሰሩ ማሰሪያ በሚመስሉ ወይም በቅርጾች ያጌጡ ስእሎችን ያያሉ።



በሮተንዳው ውስጥ የሚገኙት ሙሉ አካልን የሚያሳዩ እንዲሁም ከአንገት በላይ የሚያሳዩ ሀውልቶች በአንቶኒ ሁዶን የተሰራው የጆርጅ ዋሽንግተን ሀውልትን ጨምሮ በዋናነት የፕሬዝዳንቶች ሀውልቶች ናቸው። በእምነ በረድ የተሰራው የአብርሀም ሊንከን ሀውልት የተሰራው መንግስት ሀውልቱን እንድትሰራ የመረጣት የመጀመሪያዋ ሴት የሥነ ጥበብ ባለሙያ በሆነችው ቬኒ ሪም ነው። በሮተንዳው ውስጥ በመታሰቢያነት የሚገኙ ሌሎች የፕሬዝዳንቶች ሀውልቶች የድዌይት ዴቪድ አይዘንሀወር፣ ጄምስ ጋርፊልድ፣ አሊስስ ኤስ ግራንት፣ አንድሪው ጃክሰን፣ ቶማስ ጄፈርሰን፣ ሮናልድ ሬገን እና የጄራልድ ፎርድ ሀውልቶችን ይይዛሉ። በተጨማሪም በሮተንዳው ውስጥ የሚገኙት ሀውልቶች የአሌክሳንደር ሀሚልተንን፣ የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርን እንዲሁም በተጨማሪ የሉክሬቲያ ሞት፣ የኤልዛቤት ካዲ ስታንተንን እና ሱዛን ቢ አንቶኒን የስእል ምስሎችን ይይዛል።

የጆርጅ ዋሽንግተን ሀውልት ለብሄራዊ ሀውልት ማእከል የተሰጠው በ1934 ዓ.ም በቨርጂኒያ ግዛት ነው። ጆርጅ ዋሽንግተን ያለምንም ተቃውሞ ሙሉ ድምጽ በማግኘት የተመረጡ የመጀመሪያው የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝዳንት ናቸው።



የማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ከወገብ በላይ ሀውልት በሮተንዳው ውስጥ ለእይታ የቀረበው ጃንዋሪ 16 ቀን 1986 ዓም የዶ/ር ኪንግ 57ኛ ዓመት የልደት በዓል በሚከበርበት ወቅት ሲሆን በቋሚነት በሮተንዳው ውስጥ የተተከለው በ1989 ዓም ነው።



በ1865 ዓ.ም በኮንስታንቲኖ ብሩሚዲ የተሳለው በሮተንዳው ጣሪያ መሀል  የሚገኘው አፖቲዮሲስ ኦፍ ዋሽንግተን የጆርጅ ዋሽንግተንን በክብር ወደ ሰማይ ሲያርጉ የሚያሳይ ሲሆን በጎን በኩል ነጻነትና ድል/እውቅናን የሚወክሉ የሴት ስእሎች የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ በስድስት ቡድን በተመደቡ ምስሎች የታጀበ ነው። በኖራና በጄሶ የተሰራው ስእል 4,664 ካሬ ጫማ ቦታ ይሸፍናል።

በሮተንዳው ውስጥ ጎድጎድ ካለ ግድግዳ ውስጥ ሆነው ፍሬም የተሰራላቸው ስምንት ትላልቅ  የተሳሉ ታሪካዊ ስእሎች አሉ። በ1817 ከስነ ጥበብ ባለሙያው ጆን ትሩምቡል እንዲሰሩ በኮንግረሱ የታዘዙ የአብዮታዊ ወቅትን የሚያሳዩ፡- የነጻነት አዋጅ፣ የጀነራል በርጎይን ሽንፈት፣ የሎርድ ኮርንዋሊስ ሽንፈት እና የጀነራል ጆርጅ ዋሽንግተን የወታደራዊ ስልጣን መልቀቅ ምስሎች ይገኛሉ። እነዚህ ስእሎች በሮተንዳው ውስጥ የተቀመጡት ከ1819 እስከ 1824 ባሉት አመታት ውስጥ ነው። የአራቱ የቀደምት የግዛት ግኝቶችን የሚያሳዩት የተጨመሩት ከ1840 እስከ 1855 ባሉት አመታት ውስጥ ሲሆን እነዚህም በጆን ቫንደርሊን የተሰራው የኮሎምቦስ መሬት መድረስን፣ በዊሊያምስ ፖዌል የተሰራው የሚሲሲፒ መገኘትን፣ በጆን ቻፕማን የተሰራው የፖካሆንታስ ጥምቀትን እና በሮበርት ዌይር የተሰራው የሀይማኖት ስደተኞቹ በመርከብ ላይ ሆነው የሚያሳይ ምስሎችን ይይዛሉ።



ይህ ቅብ ጁን 28/1776 የመጀመሪያው የነጻነት አዋጅ ለሁለተኛው ክፍለ አህጉራዊ ኮንግረስ በቀረበበት ወቅት የነበረውን ቅጽበታዊ ሁኔታ ያሳያል። ሰነዱ የአብዮቱ ጦርነት የተካሄደባቸውን መርሆዎች የሚገልጽ ሲሆን ለሀገሪቱ ወሳኝ ቅርስ ሆኖ ቀጥሏል። ከአንድ ሳምንት ባነሰ ጊዜ ውስጥ አዋጁ ጁላይ 4 ቀን 1976 ዓ.ም በይፋ ጸድቋል።



በጆን ትሩምቡል የተሳለው የጀነራል ጆርጅ ዋሽንግተንን ከወታደራዊ ስልጣን መልቀቅ የሚያሳየው ስእል በዲሴምበር 23/1783 ጆርጅ ዋሽንግተን ከክፍለ አህጉራዊው የመከላከያ ሰራዊት የዋና አዛዥነት ስልጣናቸው ሲለቁ በአናፖሊስ ሜሪላንድ ስቴት ሀውስ የነበረውን ሁኔታ ያሳያል። ድርጊቱ በወታደራዊ አገዛዝ ምትክ የሲቪል ስልጣንን ለማቋቋም ወሳኝ የነበረና ለአሜሪካ መሰረታዊ የዲሞክራሲያዊ መርህ ጉልህ ሚና አለው።



የጀነራል በርጎይን መማረክ



የሎርድ ኮርንዋሊስ መማረክ



የኮሎምበስ መድረስ



የሚሲሲፒ በደ ሶቶ መገኘት



የፖካሆንታስ ጥምቀት



የሀይማኖት ስደተኞቹ ጉዞ መጀመር

# ብሄራዊ የሀውልቶች አዳራሽ

**ብሄራዊ የሀውልቶች አዳራሽ** በተጨማሪም በቀድሞ ስሙ አሮጌው የምክር ቤቱ አዳራሽ በመባል የሚታወቀው በሮተንዳ ደቡባዊ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ሰፊ ባለ ሁለት ፎቅ ከፊል ክብ የሆነ ቤት ነው። ይህ ታሪካዊ ቦታ ለ50 አመታት (1807-1857) ያህል የዩኤስ የተወካዮች ምክር ቤት የስብሰባ ማእከል ሆኖ ያገለገለ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የብሄራዊ የቅርሳ ቅርስ ስብስብ ማእከል ዋና የማሳያ ቦታ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። ይህ ስብስብ በእያንዳንዱ ግዛት ለመታሰቢያነት የተሰጡ በግዛቶቹ ታሪክ ውስጥ መዘከር የሚገባቸው ታዋቂ ሰዎችን ሀውልቶች ይይዛል። በአሁኑ ወቅት ማእከሉ በጠቅላላው በ50 ግዛቶች የተሰጡ 100 ሀውልቶችን ይይዛል። ሁሉም ግዛቶች እያንዳንዳቸው ሁለት ሀውልቶችን አዋጥተዋል።

በካፒቶሉ ውስጥ ከሚገኙ እጅግ ውብና ሳቢ ሀውልቶች ውስጥ አንዱ ወደ ካፒቶል ሮቱንዳ ከሚያስገባው በር በላይ የተቀመጠው በካርሎ ፍራንዞኒ የተዘጋጀው የታሪክ መኪና በመባል የሚታወቀው ነው። ይህ የኒዎ ክላሲካል የእምነበረድ ሀውልት የሚያሳየው ጽሁፍ ሲሊዮ ዘ ሚዩዝ ኦፍ ሂስትሪ በግዜ ሰረገላ ላይ በመሆን በምክር ቤቱ ቻምበር በነበረው ውስጥ የሚካሄዱትን ታሪኮች ስትመዘግብ ያሳያል። የሰረገላው ቸርኬ በሲሞን ዊላርድ የተሰራውን የቻምበሩን የግድግዳ ሰዓት ይዟል። ምንም እንኳ የተወካዮች ምክር ቤት የስብሰባ ቦታ በ1857 ወደ ሌላ ቦታ የተዛወረ ቢሆንም የግድግዳ ሰዓቱ አሁንም ወደ ምክር ቤቱ ቻምበር በሚያስገባ መግቢያ ትይዩ ተቀምጧል።



ፎቶግራፉ አንሺው በስም ተጠቅሶ እስካልተጸፈ ድረስ ፎቶግራፎች በሙሉ የተነሱት በዩኤስ ካፒቶል አርክቴክት ነው።

# ከጉብኝቱ በኋላ



### የትእይንት አዳራሽ

ጉብኝትዎን ካጠናቀቁ በኋላ በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከሉ የታችኛው ወለል የሚገኘውን የትእይንት ማእከል የሚጎበኙበትን ሁኔታ ያጢኑ። ይህ በሀገሪቱ ውስጥ የኮንግረሱን እንዲሁም የዩኤስ ካፒቶልን ግንባታ ታሪክ ለመግለጽ የተዘጋጀ ብቸኛ ማእከል ነው። ከትእይንት ማብራሪያዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ከብሄራዊ የሰነድ ማስቀመጫ እና የኮንግረሱ ቤተ መጻህፍት የተወሰዱ ሌላ ቦታ የማይገኙ ታሪካዊ ሰነዶችን፣ ከመላው ሀገሪቱ የተሰበሰቡ የእደ ጥበብ ውጤቶችን እና 11 ጫማ ቁመት ያለው በእጅ ሊነካ የሚችል የካፒቶሉ ጉልላት ሞዴልን ይይዛሉ። በተጨማሪም በጆሮ ማዳመጫ የሚደመጡ በሌሎች ቋንቋዎች የተዘጋጁ የትእይንት ማእከሉ የድምጽ መግለጫዎች በኖርዝና በሳውዝ ኢንፎርሜሽን ዴስኮች ይገኛሉ።

በትእይንት አዳራሹ ወይም በሴኔቱና በምክር ቤቱ የጎብኚዎች ሰገነቶች ውስጥ **ፎቶ ግራፍ ማንሳት አይፈቀድም።**

### ኮንግረስ በስራ ላይ እያለ መመልከት

ሴኔቱና የህውስ የጎብኝዎች ሰገነቶች ከሁለቱ አካላት አንደኛው በስራ ላይ በሚሆንበት በየትኛውም ጊዜ ለጎብኚዎች ክፍት ናቸው፤ ሆኖም ሰገነቶቹ በዩኤስ ካፒቶል ጉብኝት ውስጥ አይካተቱም። የመግቢያ ፍቃዶች የሚያስፈልጉ ሲሆን የውጭ ሀገር ጎብኚዎች በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከሉ የላይኛው ወለል ላይ ከሚገኙት የምክር ቤቱና ሴኔቱ የቀጠሮ ዴስኮች የመግቢያ ፍቃዶችን ሊያገኙ ይችላሉ። ምክር ቤቱ በስራ ላይ በማይሆንበት ወቅት የይለፍ ፍቃድ ያላቸው ጎብኚዎች በምክር ቤቱ ሰገነት ከጠዋቱ 03፡00 እስከ ከሰዓት 10፡15 ገብተው እንዲጎበኙ ይፈቀድላቸዋል። ሴኔቱ በስራ ላይ በማይሆንበት ወቅት የሴኔቱ ሰገነት ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ሳምንት ሴኔቱ አስቀድሞ በታቀዱ እረፍት በሚወጣበት ጊዜያት የይለፍ ፈቃድ ያላቸው ጎብኝዎች ከጠዋቱ 03፡00 እስከ ከሰዓት 10፡15 ባለው ግዜ ውስጥ ገብተው መጎብኘት ይችላሉ። የሁለቱም ሰገነቶች መግቢያ በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከል የላይኛው ወለል ላይ ይገኛሉ።

### የስጦታ እቃ መሸጫ ሱቆችና ሬስቶራንት

በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከሉ የላይኛው ደርብ ላይ የሚገኙት ሁለት የስጦታ መሸጫ ሱቆች በካፒቶሉ ሥነ ጥበብና አርክቴክቸር የተዘጋጁ የተለያዩ በልዩ ሁኔታ የተመረጡ የሚሸጡ ቅርሳ ቅርሶችን ያቀርባሉ። ሁሉም ቅርሳ ቅርሶች ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የተሰሩ ናቸው። የካፒቶሉ ካፌ የጎብኚዎች ማእከል ሬስቶራንት በካፒቶሉ የጎብኚዎች ማእከሉ የታችኛው ደርብ ላይ የሚገኝ ሲሆን እዛው የሚዘጋጁ ሾርባዎችን፣ ሰላጣዎችን፣ ጣፋጭ ምግቦችንና ለስላሳ መጠጦችን ያቀርባል።

### ማስታወሻ

እባክዎ በጉብኝቱ የቆይታ ጊዜ ውስጥ **ከተመደበልዎ የጉብኝት መሪና ቡድንዎ ጋር አብረው መቆየት** አስፈላጊ መሆኑን ያስታውሱ። ድንገተኛ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት የጉብኝት መሪዎ ከዩኤስ ካፒቶል ፖሊስ የሚሰጡትን መመሪያዎች በመቀበል ያስተላልፋሉ።

## ምስጋና!

የዩኤስ ካፒቶልን ስለጎበኙ እናመሰግናለን! ከመረጃ ዴስኮችና በካፒቶል የጎብኚዎች ማእከሉ የመግቢያና መውጫ በሮች አጠገብ እንዲሁም በድረ ገፅ www.visitthecapitol.gov በመጎብኘት በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የተለያዩ በራሪ ጽሁፎችን ያገኛሉ።

የዩኤስ ካፒቶል ጉብኝቶች በጊዜያዊነት እንዲተላለፉ ወይም የጉብኝት ሁኔታ እንዲሻሻል የሚደረግበት ሁኔታ አለ።

U.S. CAPITOL
የጉብኝት ማዕከል

www.visitthecapitol.gov